**የህግ አዋቂ እርዳታ ያስፈልግዎታል?**

ስልክ ቁጥራችን (ክፍያ የለበትም) 1-800-750-5353 ሲሆን፣ የስራ ሰዓታችን
ከሰኞ እስከ ሐሙስ ከጠዋቱ 3 ሰዓት (በዚህ ሀገር 9 ኤ. ኤም.) እስከ 11 ሰዓት (በዚህ ሀገር 5 ፒ. ኤም.)ና ዓርብ ከጠዋቱ 3 ሰዓት (በዚህ ሀገር 9 ኤ. ኤም.) እስከ 10 ሰዓት (በዚህ ሀገር 4 ፒ. ኤም.)ነ

አማርኛ በነፃ የሚያስተረጉሙ ሰዎች አሉን ነከአስተርጓሚዎቹ ጋራ እስክናገናኛችሁ አንድ ሁለት ደቂቃዎች ሊወስድብን ይችላልና ታገሱንነ ከቻሉ በሚደውሉበት ጊዜ አማርኛ እናገራለሁ ብለው በእንግሊዝኛ (አይ ስፒክ አምሃሪክ) ብለው ይናገሩና ጥቂት ደቂቃዎች ከአስተርጓሚዎ ጋራ እስክናገናኝዎ ይጠብቁነ እናመሰግናለንነ

**የምንሰጠው አገልግሎት በሙሉ ያለ ክፍያና ጉዳይዎን በምስጢር በመጠበቅ ነውነ**

## የኛ ተልዕኮ

**በሜይን ስቴት ለሚኖሩ 60 እና ከዚያ በላይ ዕድሜ ላላቸው አዛውንቶች ምርጥ የሆነ የሕግ አገልግሎት ያለ ክፍያ መስጠት ነውነ**

# የሕግ አገልግሎት ለአዛውንቶች

**ከ1974 ጀምሮ በሜይን ስቴት ለሚኖሩ አዛውንቶች የቆመ ድርጅት**

**1-800-750-5353**

**አስተርጉሚዎች አሉን**

**በሜይን ስቴት በተለያዩ ስፍራዎች ቢሮዎች አሉን**

**የምንሰጠው አገልግሎት በሙሉ ያለ ክፍያና ጉዳይዎን በምስጢር በመጠበቅ ነውነ**

Amheric - October 2001

## የህግ አገልግሎት ለአዛውንቶች ምንድን ነው?

የሕግ አገልግሎት ለአዛውንቶች (ወይንም LSE) በትርፍ ላይ ያልተመሰረተ (non-profit) ድርጅት ነው፣ በሜይን ስቴት ውስጥ ለሚገኙ ዕድሜያቸው 60 ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ አዛውንቶች ነፃ የሲቪል (ወይንም የፍትሐ ብሔር) ሕግን የተከተለ ዕርዳታና አገልግሎት መስጠት ነው፣ የአዛውንቶችን ክብርና ነፃነት ለመጠበቅ ቃል እንገባለን፣

## የህግ አገልግሎት ለአዛውንቶች(LSE) በምን በኩል ሊረዳዎት ይችላል ?

የሕግ አገልግሎት ለአዛውንቶች (LSE) ሊረዳዎት የሚችላቸው ጉዳዮች እርስዎ ባለዎት ጉዳይ ላይ የተመሠረተ ይሆናል፣ ከዚህ የሚከተሉትን ልናደርግልዎት እንችላለን ፣

- ✓ ያለዎትን ጥያቄ መመለስና ሕጋዊ ምክር በስልክ መስጠት
- ✓ እንደ ጉዳዩ ዐይነት ታይቶ፣ በእርስዎ ምትክ ሌሎችን ስለ ጉዳይዎ ማነጋገር
- ✓ ለአንዳንድ ጉዳዮች ከእርስዎ ጋሬ ፊት ለፊት መነጋገር
- ✓ እንደ ጉዳዩ ዐይነት ታይቶ ለጉዳይዎ ፍርድ ቤት መቅረብ

እኛ ልንረዳዎት ካልቻልን ሊረዱዎት ለሚችሉ እንመራዎታለን፣

## የሕግ አገልግሎት ለአዛውንቶች (LSE) በምን ዓይነት ጉዳዮች ሊረዳዎት ይችላል ?

ከዚህ በታች ባሉት ጥያቄዎች፣ ሕጋዊ ችግሮች እና ለመሳሰሉት ጉዳዮች ሊረዳዎት ይችላል፣

- ✓ የሚያስፈልግዎትን የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ (ሜዲኬይድ እና ሜዲኬር)
- ✓ በዘመድ፣ በጓደኛ ወይም በሌላ አጭበርባሪ አፈ ጮሌ በመታለል ሀብትና ንብረትዎን ቢያጡ
- ✓ ለምግብ (የምግብ ቲኬት)፣ በክረምት ጊዜ ለቤት ማሞቂያ፣ የግብር ፋታ፣ በሐኪም ትዕዛዝ ብቻ መገዛት ለሚችሉ መድኃኒቶች እና ለመሳሰሉት ከመንግሥት በሚሠጡ የዕርዳታ ፕሮግራሞች ጋር በተያያዘ ችግር ካለብዎት
- ✓ አእምሯዊና አካላዊ ጉስቁልና የሚያደርስብዎት ካለ
- ✓ ስለውክልና እና በሕይወት ሳሉ ለራስዎ መናገር ባይችሉ ምን እንዲደረግ እን ደሚፈልጉ ስለሚገልፅ ኑዛዜ ጥያቄ ካለዎት
- ✓ የመኖሪያ ችግር ካለብዎት፣ ለምሳሌ ከመኖሪያ ቤትዎ ቢባረሩ

ያልተከፈለ ሒሳብ ወይም ዕዳ ካለብዎትና የዕዳ አስከፋዮች ችግር ካለብዎት

---

**ኢንተርኔት ካላችሁ አድራሻችን www.mainelse.org ነው፣**